የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ — መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 32
ADDIS ABABA – 8th April, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፷፱/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ከኢጣልያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፭፻፰

## CONTENTS

Proclamation No. 69/1997
The Investment Promotion and Protection Agreement with the Government of the Republic of Italy Ratification Proclamation ........................... Page 508

### አዋጅ ቁጥር ፷፱/፲፱፻፹፱

### ከኢጣልያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት እና በኢጣልያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት ታህሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው የማጽደቂያ ሰነዶች ልውውጥ ከተደረገበት ዕለት አንድ ወር በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ ስለተመለከተ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከኢጣልያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፱/፲፱፻፹፱·" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 69/1997

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE INVESTMENT PROMOTION AND PROTECTION AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF ITALY

*WHEREAS*, an Agreement between the Transitional Government of Ethiopia and the Government of the Republic of Italy, on the Promotion and Protection of Investments was signed in Addis Ababa on the 23rd day of December, 1994;

*WHEREAS*, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force one month after the date of exchange of the instruments of ratification;

*WHEREAS*, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 8th day of April, 1997;

*NOW, THEREFORE*, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Republic of Italy Agreement on Investment Promotion and Protection Ratification Proclamation No. 69/1997."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትና በኢጣልያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት ታህሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል ።

፫. <u>የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on the Promotion and Protection of Investments signed in Addis Ababa on the 23rd day of December, 1994 between the Transitional Government of Ethiopia and the Government of the Republic of Italy is ratified.

3. *Power of the Ethiopian Investment Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of April, 1997.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE